**ADDA BILISUMMAA OROMOO**

**OROMO LIBERATION FRONT** جبهة تحرير اورومو

Gaafa: 31/12/2017
Date: تاريخ

Lakk.: 023/stm/abo/2017
No.: رقم

## ኣዲሱን ዓመት(2018) በማስመልከት ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር የተላለፈ መልእክት

**ለሃገር ባለቤትነት የነጻነት ትግል በማፋፋም ላይ የምትገኘው ክቡር የኦሮሞ ህዝብ፣**

**ለባርነት ፍጻሜ ለማበጀት ጠላትን በማርበድበድ ላይ ለምትገኘው ቄሮ ቢሊሱማ ኦሮሞ፣**

**የኦሮሞን ህዝብ የትግል ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ከጠላት ጋር በትንቅንቅ ላይ ለምትገኙት ለኦነግ ኣባላት በሙሉ፣**

**የህዝባችንን ጠላት በሁሉም ኣቅጣጫ በመፋለም ላይ ለምትገኘው ለኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት፣**

**በጠላት ወህኒ ቤቶች በመሰቃየት ላይ ለምትገኙት የኦነግ ኣባላትና ለሌሎችም የኦሮሞ ተወላጆች**

**እንዲሁም ለኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ኣጋሮች፡**

2017ዓም ተጠናቅቆ የኣዲሱን ዓመት መግቢያ ምክንያት በማድረግ ኦነግ በድርጅቱ የማዕከላዊ ኮሚቴ ኣባላት፣ በኦሮሞ ነጻነት ሰራዊትና በመላው የኦነግ ኣባላት ስም የእንኳን ኣደረሳችሁ መልእክቱን ሲያስተላልፍ ከታላቅ ክብርና ደስታ ጋር ነው። ኣዲሱ ዓመትም የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል በድል ተቋጭቶ ነጻነታችንን የምንጎናጸፍበት እንዲሁም ተጨቋኝ ህዝቦች ከጨቋኙና ኣፋኙ የወያኔ ስርዓት ነጻ የሚወጡበት ዓመት እንዲሆን ያለንን ምኞት እንገልጻለን።
በተጠናቀቀው ዓመት የኦሮሞ ህዝብ እንዲሁም ሁሉም ተጨቋኝ ህዝቦች ሲያካሄዱት በነበረው መራር ተጋድሎ ባስመዘገቧቸው ድሎች የወያኔ/ሕወሃት መንግስት ጸረ-ህዝብና ኣሸባሪ መሆኑን ዓለም እንዲገነዘበው ኣድርገዋል። እነዚህን የተገኟቸውን ድሎች ለማስመዝገብም የኦሮሞ ህዝብና የኢትዮጵያ ኢምፓዬር ተጨቋኝ ህዝቦች በተለያየ መልኩ ውድ መስዋዕትነቶችን ለመክፈል መገደዳቸው ተስተውሏል። በተለይ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ነጻነቱን ለመጎናጸፍና በሃገሩ ላይ ባለቤት ለመሆን ሲያካሄድ በነበረው ትግል ከባድ መስዋዕትነት ሲከፍል ነበር። ከህጻናት እስከ ኣዋቂ፣ እናቶችና ኣባቶች ሳይቀሩ ለዚህ ትግል ህይወታቸውን ኣሳልፈው ሰጥተዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በሕቡእ የተደራጁ የኦነግ ኣባላትና ቄሮ ቢሊሱማ ባካሄዱት መራር ፍልሚያ በከፈሉት ከባድ መስዋዕትነት ያስመዘገቡት ድል የነጻነት ትግሉን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ኣሸጋግሮታል። የጠላት ጎራ በትግሉ ተፈረካክሶ በየድርጅቱ ውስጥና በኢህኣዴግ ድርጅቶች መካከል ፍጥጫና ግጭት እንዲባባስ ኣድርጓል። በውስጣቸውና እርስ በርሳቸው በተቃውሞ እንዲጠመዱ በማድረግም የጠላት ጎራ መጠገን በማይቻልበት ደረጃ እንዲያሽቆለቁል ኣድርጓል።

የወያኔ/ኢሕኣዴግ መንግስት በህዝቦች ትግል በመከበቡ እንደቀድሞው ያለጥርጥር ኣገዛዙን በትዕዛዝ ማስቀጠል እንደማይችል ተረጋግጧል። ከዚሁ ጋር በወያኔ ላይ የተካሄደው የህዝቦች ትግል የወያኔ መንግስት ለህዝቦች ጥያቄ ምላሽ መስጠት የማይፈልግ ጸረ-ህዝብ መሆኑን ግልጽ ለማድረግ መቻሉ በተገኙት ድሎች ውስጥ ይጠቀሳል።

ጸረ-ህዝቦች የሆነውን መንግስት በመጋፈጥ ለማስወገድ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በ2017ዓም ውስጥ ከወሰዳቸው እርምጃዎች መካከል ኣንዱ የኦነግ ድርጅታዊ ጉባዔ በማካሄድ ጠንካራ ኣመራር ማስገኘት ነበር። እንደ ድርጅት እራሱን ማጠናከር ወሳኝ በመሆኑ በተካሄደው 4ኛው የኦነግ ድርጅታዊ ጉባዔ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በሃገር ቤት እየተካሄደ ባለው የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ውስጥ ከጠላት ጋር በመተናነቅ ላይ ያሉትንና ጉልህ ድርሻ ያላቸውን ጨምሮ ኣመራር በመምረጥ ጉባዔውን በስኬት ኣጠናቋል። ጠላትና የትግሉ ጸሮች ይህ ጉባዔ እውን እንዳይሆን ያደረጓቸው ጥረቶች በትግል ከሽፎ ጉባዔውን በማካሄድ ኦነግ ይበልጥ ተጠናክሯል። በድርጅቱ ዓላማ ላይ የተመሰረተ የትግል መመሪያ በማጽደቅና ትግሉን ወደ ፊት ለማራመድ በተላለፉ የተለያዩ ውሳኔዎች ላይ በመመርኮዝ የተከናወኑት ስራዎችም ጠላትና ኣጫፋሪዎቹን ኣንገት ያስደፉ ናቸው። ከኦሮሞ ህዝብ ውጪ ያለኣንዳችም ኣጋዥ በራስ ላይ በመመርኮዝ እየተካሄደ ያለው ይህ የነጻነት ትግል የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ጠላቶችና ደንቃራዎችን ከማስወገድ ኣልፎ እንዲፈረካከስ ማድረጉ ባሳለፍነው ዓመት ከተገኙት ድሎች ውስጥ ይቆጠራል።

የወያኔን መንግስት በስልጣን ላይ በማንሰበት ጥቅም የሚያገኙ የጎረቤት ሃገራትና ሌሎችም መንግስታት የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግልን ለማደናቀፍ ከተሰለፉት ውስጥ ይመደባሉ። በዚህ ረገድ የነጻነት ትግሉ እንዳይሰማና እንዳይታይ ለማፈን ያደረጉት ጫና ከባድ መሆኑ ኣይካድም። ይህንን ማሸነፍ የሚቻለው በራስ ላይ በመመርኮዝ ብቻ መሆኑን የተገነዘቡት የኦነግ ኣባላትና ደጋፊዎች፣ ቄሮ ቢሊሱማና የኦሮሞ ብሄርተኞች ባካሄዱት ያልተቋረጠ ትግል የጠላት ዓላማ ከሽፎ የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ሊታፈን ከማይቻልበት ደረጃ እንዲደርስ ኣድርገዋል። እስከ ኣሁንም የነጻነት ትግሉ ዋነኛ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኗል። የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተቋማትም እየተፋፋመ ባለው ትግል ውስጥ በወያኔ እየተፈጸመ ያለውን የጭካኔ ድርጊት ከመዘገብ ኣልተቆጠቡም። የወያኔ መንግስት ጸረ-ዲሞክራሲና ኣሸባሪ መሆኑ በስፋት እንዲዘገብ ያደረገው የኦሮሞ ህዝብ በግንባር ቀደምትነት እያካሄደ ያለው ህዝባዊ የነጻነት ትግል ነው።

ኦነግ ከምስረታው ኣንስቶ እስከ ኣሁን ድረስ የኦሮሞ ህዝብን ኣንድነት እውን እንዲሆን ሰፊ ስራ ሰርቷል። ጠላት ይህ የተቀደሰ ዓላማ እውን እንዳይሆን የተለያዩ እንቅፋቶችን ሲፈጥርና ጥቃቅን ልዩነቶችን በማራገብ የኦሮሞን ኣንድነት ለማፈራረስ ያደረገው ጥረትም እንደሌሎቹ የጠላት ዓላማዎች ሁሉ እንዲከሽፍ ተደርጓል። በተለይም ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ ኣንድነት እንደጸሃይ በርቶ በመታየቱ ጠላትን ውጥረት ውስጥ ከቷል። ምስጋና ለታጋዮችና ብሄርተኞች ይሁንና በኦነግ በሚመራው የነጻነት ትግል የኦሮሞ ህዝብ ኣንድነት ሊረጋገጥ ችሏል። ዛሬ ኦሮሞን መለያየት ፈጽሞ የማይቻል ሆኗል።

ኦሮሞን በማፈናቀል የሃገሩን ጂኦግራፊና ዲሞግራፊ መቀየርን ፖሊሲው ያደረገው ጠላት በኦነግ በሚመራው የነጻነት ትግል በተለይ ደግሞ በኦነግ ስር በተደረጀው ቄሮ ቢሊሱማና በኦሮሞ ብሄርተኞች ትግል ሊመከን የቻለው፡ የጸረ-ጭቆና ኣመጽን ወደ የጭቆና ፍጻሜ ኣመጽ በማሸጋገር መሆኑ ኣይካድም። የኦሮሞ ህዝብ በኣንድነት ተሰልፎ ለሃገሩ እንዲፋለም ለማስቻል የተሰራው ስራ ሊሳካ የቻለው የኦሮሞ ህዝብ በኣንድነት በመነሳቱና ታጋዮች በከፈሉት መስዋእትነት ስለሆነ የላቀ ምስጋናና ክብር ይገባቸዋል። ይህም ትግሉ ያስመዘገበው ታላቁ ድል ሆኖ ሲታወስ ይኖራል።
የወያኔ/ኢሕኣዴግ መንግስት በህዝቦች ይሁንታ ስልጣን ላይ ኣልወጣም። ወደ መንበረ-ስልጣን የመጣው በሃይል ነው። በሃይልም ስልጣን ላይ ሰነበተ። ስልጣኑንም በጦርና በደህንነት ሃይሉ ላይ በመመርኮዝ እያስጠበቀ ይገኛል። በተለይ ደግሞ እስከ ቀበሌ የተዋቀረው የደህንነት ሃይሉ መረብ የስርዓቱን ኣገዛዝ ለማራዘም ከፍተኛ ድርሻ ኣለው። ይህ የወያኔ መንግስት መዋቅር የኦሮሞን ህዝብ ከመቆጣጠር ባሻገር ጸረ-ነጻነት ትግል በመሆን ለኦሮሞ ህዝብ መብት መከበር እንቅፋት ሆኗል። ዛሬ የወያኔ መንግስት ተመርኩዞበትና ተማምኖበት ሲኖር የነበረው መዋቅር በትግል ዳሽቋል። በኦሮሚያ ውስጥ የተዘረጉት የጠላት መዋቅሮች ኣብዛኛዎቹ ተሽመድምደዋል። ተታልለውም ሆነ ለጊዜያዊ ጥቅም ሲሉ በኦሮሞ ህዝብ ላይ እኩይ ተግባር ሲፈጽሙ የነበሩት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ተደርገዋል። ይህንን ትግሉ ያስገኘውን ድል እያስጠበቁ ጠላት መልሶ በሁለት እግሩ እንዳይቆም ለማድረግ በቀጣይነት መስራት ይኖርበታል።

የኦሮሞ ህዝብ በትግሉ ድል ያደረገው ሌላው የጠላት ሴራ የነጻነት ትግሉ በወያኔ ኣጋሮች ላይ ያስመዘገበው ድል ነው። የወያኔ መንግስት ኦሮሚያ የኦሮሞ ህዝብ የሚከብርበት፣ ሰርቶ የሚኖርበት ሃገር ሳይሆን ኦሮሞ በድህነት የሚማቅቅበትና የሚፈናቀልበት እንዲሆን ሰርቷል። ይህን ይበልጥ የሚያረጋግጠው ባጠናቀቅነው ዓመት ውስጥ በኦሮሚያና ከኦሮሚያ ውጪ የተፈጸሙት ጠላታዊ እርምጃዎች ናቸው። ስርዓቱ የኦሮሞን ህዝብ ከሃገሩ ኦሮሚያ ከማፈናቀሉም በተጨማሪ ለረጅም ዓመታ በሰላምና በወንድማማችነት ኣብሮት ከኖረው ህዝብ ውስጥ የኦሮሞ ዜጎች እንዲባረሩ በማድረግ ማፈናቀሉ ነው። ይህ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተወሰደው ዘግናኝ እርምጃ በኦሮሞ ህዝብና በሶማሌ ህዝብ መካከል መቸውም የማረሳ ጠባሳ ፈጥሯል። ልዩ ሃይ በሚል ስም በወያኔ ተመስርቶ ከመንግስት ጦር ድጋፍ፣ ስልጠናና ሙሉ ትጥቅ ተሰጥቶት በመሳሪያ-ኣልባ ሰላማዊ የኦሮሞ ህዝብ ላይ የዘመተው ይህ ሃይል፡ እጅግ ኣሰቃቂ እርምጃ የወሰደው የጠላትን እኩይ ዓላማ ለማሳካትና የኦሮሞን ህዝብ ሃብትና መሬት ለመቆጣጠር ከማለም ነው።

ዛሬ ተስፋፍቶ እየታየ ያለው ይህ ዘመቻ ለለፉት 26 ዓመታት ሳይቋረጥ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ሲካሄድ የነበረ መሆኑ ኣይዘነጋም። የኦሮሞ ህዝብ የተከፈተበትን ሰፊ ዘመቻ በጥንካሬና በኣንድነት መመከት መቻሉ የሚደነቅ ነው። ይሁን እንጂ የወያኔ መንግስት ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ በኦሮሚያና በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያነጣጠረው ይህ ጦርነት ቀጣይ ነው። በኦሮሞ ህዝብ ህልውና ላይ ያነጣጠረውን ዘመቻ ይበልጥ ለማክሸፍ የኦሮሞ ህዝብ ኣንድነቱን እያጠናከረ ጠላትን መጋፈጡን መቀጠል ይኖርበታል።

የኦሮሞ ህዝብ ጠላት የኦሮሞን የነጻነት ትግል ለማምከን ያተኮረበት ሌላው በሃገር ቤት ያለውን የኦነግ መዋቅርና የቄሮን ንቅናቄ መቆጣጠር ላይ ያለመ ነበር። ይህም ጠላትን ብቻ ሳይሆን ላለፉት 26 ዓመታት ለወያኔ ሲላላኩ የነበሩትንና እራሳቸውን ሆነው መታየት ያልቻሉትን፣ የጠላት ኣገልጋይ ሆነው ለመኖር የመረጡትን ያካትታል።

የኦነግ መዋቅር፣ ቄሮና የኦሮሞ ወጣቶች ይህንን የጠላት ዘመቻ በመጋፈጡ ውስጥ የከፈሉት መስዋዕትነት ዘወትር በታሪክ የሚታወስ ነው። በከፈሉት መስዋዕትነትም የድርጅቱንና የወጣቶችን መዋቅር ኣስጠብቀዋል። ይህ በኦሮሞ ወጣቶች ላይ የተከፈተው ዘመቻም የኦሮሞ ወጣቶችን እርስ በርስ የማናቆር ሴራ ያዘለ ነው። **ፎሌ** በሚል የሚታወቀው ባህላዊ ተቋም ስም በመስረቅና ከዓላማው ውጪ የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ ለማድረግ በጠላት ጀሌዎች የተደረገው ጥረት የኦሮሞ ወጣቶችን እርስ በርስ ለማጋፈጥ የታቀደ እኩይ ተግባር ነው። ፎሌ በህዝቡ ላይ ሳይሆን ለህዝቡ ደሕንነት የሚሰራ የባህል ኣደረጃጀት መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ኦፒዲኦ እኩይና ኣስነዋሪ ዓላማ በመያዝ ለህዝቡ መስዋዕትነት እየከፈሉ ያሉትን የኦሮሞ ወጣቶች፥ ቄሮ ቢሊሱማን ፎሌን በማደራጀት ለማንበርከክ ሲሞክር እንደነበርና ኣሁንም እየሞከረ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው። ይህ ድርጊት የጠላትን ተልዕኮ ከግቡ ለማድረስ የሚደረግ ጥረት መሆኑን በመገንዘብ ኣባገዳዎች፣ እንዲሁም የኦሮሞ ወጣቶች ኦፒዲኦ ሊገለገልባቸው በጥረት ላይ ያለውን “ፎሌ” ለፖለቲካ ዓላማቸው ብቻ መሆኑን በመገንዘብ በማረም ላይ እንዲሰሩ ኦነግ መልእክቱን ያስተላልፋል። ህዝባችንም ይህንን ዓላማ ለማክሸፍ ከልጆቹ ጎን መቆም ኣለበት። ከዚሁ ጋር ለግል ጥቅማቸው ሲሉ በታጋዮች ላይ እየዘመቱ ያሉ ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ኦነግ ምክሩን ይለግሳል። ጊዜው ከጠላት ጋር በማበር በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚዘመትበት ሳይሆን ከኦሮሞ ጎን ተሰልፎ ለወገን የምንሰለፍበት ጊዜ መሆኑን ኦነግ ያሳስባል።

ባሳለፍነው ዓመት ከወያኔ መንግስት በተጨማሪ በቡድንም ይሁን በግለሰብ ከጠላት ጋር በማበር ለኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ዓላማ እንቅፋት መሆንን የመረጡ ሃይሎች የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን ስም ለማጥቆር ያካሄዱት ዘመቻ ሰፊ ነበር። እነዚህ ትናንሽ ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት የሚሯሯጡት ኣካላት ኦነግና የኦሮሞን ህዝብ ለመነጣጠል ጥረት ኣድርገዋል። ይሁን እንጂ ዛሬ የኦሮሞን ኣንድነትና የነጻነት ትግሉን መሰረት ለማስያዝና ከጠላት ዘመቻ ታድጎ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ለማድረስ የ40 ዓመታት መስዋዕትነት የከፈለውን ኦነግ እንዲሁም ቄሮና ኦነግ ኣንድ መሆናቸውን ኣምኖ ባለመቀበል የጠላትን ተልእኮ ለማሳካት ያካሄዱት ፖሮፓጋንዳ ኦነግን ኣጠናከረው እንጂ ከህዝቡ ሊነጥለው ኣልቻለም። ኣሁንም ቢሆን ከተያያዙን ኣፍራሽ ተግባር እራሳቸውን ባለመቆጠብ ለህዝቡ የወገኑ በመምሰል የጠላትን ተልዕኮ ማስተላለፍ በመቀጠላቸው በሃገር ቤትና በውጪ ሃገራት ያለው ህዝባችን መከላከል ብቻ ሳይሆን ዓላማቸውን በማክሸፉ ላይ በርትቶ እንዲሰራ ኦነግ ያሳስባል።

ኦነግ የኦሮሞም ይሁን ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች በመመስረታቸው ላይ ተቃውሞ ይሁን ጥላቻ የለውም፥ ኖሮትም ኣያውቅም። መደራጀት መብት ነው። ይሁን እንጂ ኣንዳንድ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በጠላት ላይ ትግል የማካሄድ ሳይሆን ኦነግን ቢቻል የማጥፋት፡ ካልሆነም የማዳከም ዓላማን ያነገበ ነው። ይህ ዓላማም የግል ጥላቻ፣ የስልጣን ጥማትና ኦነግ ካልጠፋ በስተቀር ተሰሚነት ኣይኖረንም ከሚል ጭፍን ሃሳብ ይመነጫል። በ”ኢትዮጵያ” ስም የተደራጁት የፖለቲካ ድርጅቶችም ኦነግን የማፍረስና የማጥፋት ቋሚ ዓላማ ኣንግበው እንደሚንቀሳቀሱ የማያውቅ የኦሮሞ ዜጋ ጥቂት ነው። የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን በማጥፋት የኦሮሞን ህዝብ ጥያቄ ማፈን ዓላማቸው ነው። ኦነግና የኦሮሞ ህዝብ መስዋዕትነት እየከፈሉለት ያለው የኦሮሞ የነጻነት ትግል በነዚህ ድርጅቶች እይታ የዲሞክራሲ መብት ሳይሆን ሃገር የማፈራረስ ነው። ኦነግ ለየትኛውም ድርጅት መብቱን ኣክብሮ እያለ የኦነግን ኣለማክበር፣ ኣፍራሽ ፕሮፓጋንዳ መንዛትና ለማፍረስ ማሴር ኣሁንም ይሁን ለወደፊቱ የሚያስገኘው መፍትሄ የለም። ባገኙት መድረክ ላይ የኦነግን ስም ለማጥቆር መሞከር ሃላፊነትን መዘንጋትና ለህዝብ መብት ክብር ኣለመስጠት ነው። ለዲሞክራሲ መብት እንታገላለን እያሉ ለህዝባቸው ዲሞክራሲ የሚፋለሙትን በጠላትነት መፈረጅ ኣሳፋሪ ነው። ኦነግ ይህን መሰሎቹን እየመከተ ይዘውት የሚጓዙትን ዓላማም ሲያከሽፍ ዛሬ ላይ ደርሷል። ለወደፊቱም መከላከል መብቱ መሆኑን ያሳስባል።

ማንኛውም ህዝብ ከጭቆናና ብዝበዛ ነጻ ሆኖ መኖርን ይፈልጋል። በሃብቱ ላይ ባለቤት መሆን የሁሉም ህዝቦች ፍላጎትና መብት ነው። ነጻ ሆኖ መናገር፣ ያለ ተጽእኖ ወኪሉን መመረጥ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ውስጥ በስፋት የሚታይ የዲሞክራሲ መብት ነው። ይሁን እንጂ ዛሬም ቢሆን ከሕወሃት/ኢህኣዴግ መንግስት ኣገዛዝ የተነሳ የኢትዮጵያ ህዝቦች ይህንን መብታቸውን እንደተጠሙ ናቸው። ስርዓቱ በህዝቦች ትግል ውጥረት ውስጥ ሲገባ ጥቃቅን የማስመሰያ ለውጦችን በማድረግ የህዝቦች መብት የተከበረ ኣስመስሎ በመደስኮር ጭቆናና ኣፈናውን ማጠናከር የወያኔ ውሳኔ እንደሆነ ቀጥሏል።

ከዚህም እየደረሰ ያለው ጉዳት እየጨመረ በመሄድ ላይ እንዳለ፥ ለወደፊቱም ይበልጥ እየከፋ የሚሄድ መሆኑ ኣያጠራጥርም። በተለይ ደግሞ በኦሮሞ ህዝብ ላይ በማተኮር ያወጣው እኩይ እቅድ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚሸጋገር መሆኑ እየተገበረ ያለው ድርጊት በሚገባ ያረጋግጣል። ስለሆነም ኣስተማማኝ ደረጃ ላይ የደረሰውን የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ከግቡ ለማድረስ በጥንካሬ መስራት ሌላ ኣማራጭ የሌለው የታጋዮችና የህዝባችን ግዴታ ነው።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የኦሮሞን የነጻነት ትግል ለማሳካት ድርጅቱን በማጠናከር ላይ ኣተኩሮ በመታገሉ ውጤታማ ሊሆን ችሏል። በመሆኑም ኣደረጃጀቱን ይበልጥ በማጠናከርና በማስፋፋት ወደ ድል መገስገስ የኣባላትና ደጋፊዎች ግዴታ መሆኑን ኣውቀን ኣዲሱን ዓመት በድል ለመወጣት መንቀሳቀስ ይኖርብናል። የኦሮሞ ህዝብ ጠላት ከስልጣን እስካልተወገደ ድረስ የኦሮሞን ህዝብ የነጻነት ትግል ለመቀልበስ ደባ መፈጸሙን ይቀጥላል። በዚህ ኣዲስ ዓመት ሁሉንም የጠላት እቅድ በማክሸፉ ላይ በርተትን መስራት ከኛ የሚጠበቅ የዜግነት ግዴታ መሆኑን ኦነግ በዚህ ኣጋጣሚ ይገልጻል።
የድርጅታችን ኣባላትና የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በሁሉም መስክ እራሳቸውን ማጠናከር፣ የትግሉን እንቅስቃሴ ማስፋትና የድርጅቱን እቅድ ስራ ላይ ማዋል ያለባቸው የትግል ግዴታ መሆኑን በማወቅ በስፋት በመስራት የህዝባችን ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ በማድረጉ ላይ እንዲሰማሩ ኦነግ መልእክቱን ያስተላልፋል። ከዚሁ ጋር ለነጻነት ትግሉ ኣጋርና ደጋፊ በማፍራቱ ላይ በስፋት እንዲሰራም ኦነግ ያሳስባል።

የኦሮሞን ህዝብ በሃይል ከቀዬው በማፈናቀል መሬት-ኣልባ የማድረግ እቅድ ኣሁንም ቢሆን በስፋት እንደቀጠለ ነው። ፈጣን ልማትና እድገት እናስገኛለን በማለት በሚነዙት የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ኦሮሞን ከመሬቱ ኣፈናቅለው በማባረር እየከበሩ ያሉት ወያኔዎችና ከወያኔ የተሻረኩ ባዕዳን እንደሆኑ ግልጽ ነው። ኦሮሚያ የኦሮሞ ህዝብ የሚከብርበትና፣ ሰርቶ የሚኖርበት ሳይሆን ደህይቶ በረሃብ የሚሰቃይበትና ከኦሮሚያ የሚሰደድበት እንዲሆን እየተደረገ መሆኑ ከማንም የተሰወረ ኣይደለም። የዚህም ማሳያ የወያኔ መንግስት በተጠናቀቀው ዓመት ውስጥ ከኦሮሚያ ውጪ የወሰደው እርምጃ ነው።
የወያኔ/ኢሕኣዴግ መንግስት የኦሮሞን ህዝብ ከሃገሩ ኦሮሚያ ከማፈናቀሉም በተጨማሪ ለረዥም ዓመታት በሰላምና በወንድማማችነት ኣብሮ የኖረን ህዝብ ኣጋር በማድረግ የኦሮሞኝ ተወላጆች ከኣካባቢያቸው ኣፈናቅለው እንዲያባብርሩ ማድረጉ ነው። ይህ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተፈጸመው ጠላታዊ ተግባርም መቸም የማይረሳ የታሪክ ጠባሳ በኦሮሞ ህዝብና በሶማሌ ህዝብ መካከል ፈጥሯል። ንብረታቸው ተዘርፎ ለተባረሩት እነዚህ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ የኦሮሞ ዜጎች ህዝባችን ያሳየው ወገንተኝነትና ደራሽነት መላውን ኦሮሞ ያኮራ ተግባር ነው። የችግር ጊዜ ደራሽ ወገን በመሆን ከኣራቱም የኦሮሚያ ኣቅጣጫ ባደረገው ርብርብ የኦሮሞን ህዝብ ኣንድነት ይበልጥ ኣረጋግጧል። ኦነግ የኦሮሞ ህዝብ ለወገኑ ያደረገውን ይህንን ድጋፍ እያደነቀ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም ያበረታታል። ይህን መሰል ጸረ ህዝብ ድርጊት የወያኔ መንግስት ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ የሚቆም ኣለመሆኑ ከግንዛቤ ገብቶ ህዝባችን ካሁኑ በበለጠ እራሱን ለመከላከል መራጀትና መዘጋጀት የግድ ይላል።

የወያኔ/ኢሕኣዴግ መንግስት በተለይ በኦሮሞ ወጣቶች ቄሮ ቢሊሱማ ላይ በማተኮር በኦነግ ስምና በጸረ-ሰላምነት በመፈረጅ ባሳለፍነው ዓመት ውስጥ በስፋት ያከናወነው ግድያና እስራት ኣረመኔያዊ ተግባርና የኣሸባሪ መንግስት እርምጃ ነው። ከኦሮሚያ ውጪም ለትምህርት ወደ ትግራይ በሄዱት የኦሮሞ ወጣቶች ላይ እንደቀድሞው ሁሉ ባለፈው ዓመት የተወሰደው እርምጃ ይህ መንግስት ለኦሮሞ ኣንዳች ርሕራሄ የሌለውና የከፋ ኣደጋ ከማስከተል ወደኋላ የማይል መሆኑን ያሳያል። የኦሮሞ ወጣት በዚህ ኣረመኔያዊ እርምጃ  ሳይንበረከክ የኦነግን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ያሳየው ቁርጠኝነት ማንም ሃይል ከዓላማው ሊገታው እንደማይችል በሚገባ ኣሳይቷል። ቄሮ ኦሮሞ በግንባር ቀደምትነትና በቆራጥነት ባካሄደው ፍልሚያ ለህዝቡ ኣለኝታ ከመሆንም ኣልፎ ህዝቡ ከጎኑ እንዲሰለፍ ኣድርጓል። ለእስራትና ግድያ ሳይንበረከክ፣ በመደራጀት እያሳየ ያለው ኣልገዛም-ባይነት ለሌሎች ወጣቶችም ምሳሌ ሆኗል።

ዛሬ በኦሮሚያ ውስጥ “**ለወያኔ ኣንገዛም**” የሚለው መፈክር ከሁሉም የኦሮሚያ ቀበሌዎች እያስተጋባ ነው። እየተካሄደ ያለውን የጭቆና ፍጻሜ ኣመጽ በኣዲሱ ዓመት ለማሳካት “**በኣንድነት እንነሳ!**” የሚል መፈክር ከሁሉም ቦታ ይሰማል። ኣንድ ሆኖ ለመብቱ የሚፋለምን ህዝብ ሊያሸንፍ የሚችል ሃይል የለም። ይህንን እውነታ የሚጠራጠር ካለ  የጨቋኞችና ኣምባገነን መንግስታትን ታሪክ የማያውቅ ብቻ ነው።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የወያኔ መንግስት ሊያሸንፈው የማይችለውን ህዝብ እየወጋ መሆኑን እያስታወሰ፡ ሁሌም ኣሸናፊው ለመብቱ የሚፋለም ህዝብ መሆኑን ያስገነዝባል። የኦሮሞ ህዝብ እየታገለለት ያለው ዓላማ በድል እንዲቋጭም ኦነግ በሁሉም መስክ ከህዝቡ ጋር መሆኑን በኣጽንዖት ያሳስባል። በቄሮና በኦሮሞ ወጣቶች ላይ እየተወሰደ ባለው ጠላታዊ እርምጃም የጭቆና ፍጻሜ ኣመጽ የማይከስም መሆኑን የድርጅታችን ኣባላትና ደጋፊዎች እንዲሁም መላው የኦሮሞ ህዝብ በመረዳት እንደካሁን ቀደሙ እያካሄዱት ያለውን የመብት ትግል በጀግንነትና በቆራጥነት እንዲቀጥሉ ኦነግ መልዕክቱን ያስተላልፍላቸዋል።

ለረዥም ዓመታት ኦነግና የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊትን ለማጥፋት በተካሄደው ዘመቻ ኦነግና ሰራዊቱ ኣልጠፉም። ይሁን እንጂ ጠላት ኣሁንም ኦነግን ኣጠፋለሁ የሚል ከንቱ ህልም እያለመ መሆኑ እሙን ነው። ኦነግ ከውስጥና ከውጪ በሁሉም መስክ እየተካሄደበት ያለውን ዘመቻ በመመከቱና ዓላማው በህዝቡ ዘንድ ፍቅር፣ ክብርና ድጋፍ እያገኘ በመምጣቱ ህዝቡ በኣንድ ድምጽ “**ኦነግ ያስተዳድረን!፣ የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል መሪ ኦነግ ነው! የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት የኦሮሞ ህዝብ ጋሻ-መከታ ነው!**” በሚል በይፋ ኣቋሙን በመግለጽ ላይ ይገኛል። ይህን ህዝባዊ ፍቅርና ድጋፍ ያስገኘው የኣባሎችና ደጋፊዎቻችን እንዲሁም የህዝባችን መስዋዕትነት ነው። ትግሉን ለማስቀጠልና መሪ ድርጅቱን በማጠናከሩ ውስጥ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ኣያከራክርም። ኣሁንም ቢሆን የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት በከተማና በገጠር በስፋት በጠላትና ተላላኪዎቹ ላይ እየወሰደ ባለው እርምጃ የጠላትን ኣከርካሪ በመስበር ላይ ይገኛል። ይህንን በ2018 ይበልጥ በማስፋፋት ህዝቡ ከኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት የሚጠብቀውን ወደማሟላቱ እንደምንሻገር ኣንጠራጠርም። የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ይህ ግዴታው መሆኑን በመገንዘብ ይህንን ለማሟላት እንዲተጋ ኣጥብቀን እናሳስባለን።

በተለያየ ስምና ዓላማ ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኙ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳሉ ይታወቃል። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከነዚህ ድርጅቶች ጋር እርቅ በማውረድ የነጻነት ትግሉን ጎራ ለማስፋትና ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ እንደነበር ከኦሮሞ ህዝብ በተለይም ደግሞ በውጪ ሃገራት ከሚኖረው የኦሮሞ ማህበረሰብ የተሰወረ ኣይደለም። በኣንድ ድርጅትና ኣመራር ስር ተደራጅተው ትግል ለማካሄደ ከወሰኑት ጋር ለመስራት በተደረሰው ስምምነት በመዋሀድ በኣንድ ኣመራር ስር መሰባሰብ ተችሏል። የተቀሩትም እንደኣንድ ድርጅት በኣንድ ኣመራር ስር ለመስራት የሚያስችል ስምምነት ላይ ባይደረስም ቢያንስ እርስ በራሳችን ላይ ኣፍራሽ ፕሮፓጋንዳ መንዛትና መጋፈጥ ጉዳቱ እንጂ ጠቀሜታው ስለማይታይ ከዚህ ኣድራጎት ለመቆጠብ ስምምነት ላይ ተደርሷል። ስምምነቱን በመተርጎሙ ላይ ለታየው ድክመት ኦነግ ተጠያቂ እንደማይሆን ግልጽ ነው። የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶችን ጉዳይ ኣስመልክቶ የኦነግ 4ኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ባስተላለፈው ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ የድርጅቱ ኣመራር ጥሪ ሲያቀርብ እንደነበር ይታወሳል። ኣሁንም ቢሆን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በእውነትና በቅንነት የድርጅቶችን መብት እያከበሩ ኣብረን ለመስራት ዝግጁ ከሆኑ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ለመስራት መወሰኑን እያሳወቀ፡ ያሉ ድርጅቶችም ይህንን ግዴታ እንዲወጡ ያስገነዝባል። ለዚህ ጥሪም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ምላሽ እንደሚሰጡ ያለውን ተስፋ እየገለጸ ህዝባችን ለዚህ ዓላማ መሳካት የሚጠበቅበትን እንዲያበረክት ይጠይቃል። ይህንን ገንቢ ሃሳብ ለማፍረስ የሚሰሩትን ተከታትሎ እንዲያጋልጥ ኦነግ መልዕክቱን ያስተላልፋል።

ዛሬ የወያኔ እስር ቤቶች ኣንዳችም ጥፋት በሌላቸው የኦሮሞ ዜጎች ተሞልቷል። ባልታወቁ የወያኔ ወህኒ ቤቶች ውስጥ ሰቆቃ እየደረሰባቸው ያሉም ኣያሌ ናቸው። እነዚህ ለራሳቸውና ለህዝባቸው መብት ሲሉ ከፍተኛ ኣካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጥቃት እየደረሰባቸው ያሉ ዜጎች ሁሉ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ክብር ኣላቸው። የኦሮሞ ህዝብ እነዚህን ለመብቱ በመፋለማቸው ጠላት ሰቆቃ እየፈጸመባቸው ያለውን ልጆቹን መርዳቱን እንዲቀጥል ኦነግ እየጠየቀ፥ በበኩሉ ከጎናቸው መቆሙን እንደሚቀጥል ያረጋግጣል።

የኦሮሞ ህዝብ እየታገለ ያለው መብቱን የሚያስከብርለት ስር-ነቀል ለውጥ ለማስገኘት ነው። የኦሮሞ ህዝብ ትግል ስኬት የሁሉም ተጨቋኝ ህዝቦች ትግል ስኬት ነው። የኦሮሞ ህዝብ ትግል የትግራይ ህዝብን ጨምሮ ለማንኛውም ህዝብ ጠላታዊ ኣመለካከት የለውም። ይህንን ባለማወቅ የኦሮሞን ህዝብ እንደጠላት በማየት የዘመቱበት፥ ዛሬ ኣብረውት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየዘመቱት ያለው ጠላት ነገ ወደነሱ እንደሚዞር መዘንጋት የለባቸውም። የኦሮሞን ህዝብ ሰላም ነፍገው በሰላም እንኖራለን ማለት የማይታሰብ ነው። ስለሆነም ለጊዜያዊ ጥቅም ኣጋር ካደረጋቸው የወያኔ መንግስት መተባበር በማቆም እስትራቴጂያዊ ኣጋራቸው ከሆነው የኦሮሞ ህዝብ ጋር በመሰለፍ የጋራ ጠላታችንን መዋጋት የሁሉም ተጨቋኝ ህዝቦች ግዴታ ይሆናል። ለነገ ኣብሮ መኖርም ገንቢውና ኣስተማማኙ መንገድ ይህ ብቻ መሆኑን ኦነግ እያሳሰበ፡ ለዘመናት የቆየውን የህዝቦች መልካም ግንኙነት ከሚያደፈርሰው ተግባር በኣስቸኳይ እንዲገቱ ምክሩን ይለግሳል። በተጨማሪም ዘላቂ መፍትሄ የሚያስገኘው የኦሮሞን ህዝብ መብትን ኣውቆ መቀበል መሆኑንም ያሳስባል። ህዝባችን ደግሞ ከሚከፈትበት ማናቸውም ወረራ እራሱን ለመከላከል የዓለም አቀፍ ህግ እንደሚፈቅድለት ተግንዝቦ እራሱን ከጥቃት ለመከላከል ጠንክሮ እንዲሰራ በድጋሚ እናስታውቃለን።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ለሁሉም ህዝቦችና መብቶቻቸው የላቀ ክብር እንዳለው በተደጋጋሚ ገልጿል። ለዚህም በተለያዩ ጊዜያት የተሻሻሉትን የኦነግ የፖለቲካ ፕሮግራም መመልከት ይቻላል። ይህንኑ ከምስረታው ኣንስቶ በመተግበር ኣሳይቷል። ከተጨቋኝ ህዝቦች ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር ለጋራ ዓላማና ግብ ለመስራት ቃሉን እያደሰ በጠላት ተደናግረው የኦሮሞን ህዝብ የነጻነት ትግል በጥርጣሬ ኣይን ለሚያዩት የኦሮሞ ህዝብ ነጻነት እውን መሆን የሌሎችንም ህዝቦች መብት የሚያስከብር እንጂ የሚጎዳ ኣለመሆኑን ያረጋግጣል።

የወያኔ መንግስት በህዝቦች ተቃውሞ ተከቦ በፍጥነት ወደ ውድቀቱ እያመራ እንዳለ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ጸረ-ህዝብ መንግስት ኣሁንም እራሴን ኣድሼ ኣገዛዜን እቀጥላለሁ በሚል እኩይ ዓላማው የማይተገበር የውሸት ቃልና በግለሰቦች ለውጥ ህዝቦች የሚፈልጉትን ለውጥ ለማስቀረት መስራቱን ቀጥሏል። በዚህ ኣቋምም የኦሮሞ ዜጎችን መግደልና ማሰርን የዕለት ተዕለት ስራው ኣድርጓል። በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ሁኔታ እያየ፥ የኦሮሞ ህዝብን ማንነት ለማጥፋትና ትግሉን ለማፈን ያለመውን የጠላት እቅድ ኣንግቦ ከጠላት ጋር መሰልፍ ይቅርና መታየት እንኳ ኣጸያፊ በሆነበት በዚህ ወቅት የፖለቲካ ኣመራርና የጦር መኮንን በመሆን በመንግስት መዋቅር ውስጥ ታቅፎ ለጠላት መስራት በህግም ይሁን በታሪክ ያስጠይቃል። ስለሆነም ይህንን በመገንዘብ በማናቸውም የመንግስት መዋቅር ውስጥ የምትገኙ የኦሮሞ ዜጎች በተለይ ደግሞ በወያኔ ጦር ሃይል ውስጥ በተለያየ ደረጃ የምትገኙ ዜጎች ሁሉ ህዝባችሁ በተደጋጋሚ እያቀረበላችሁ ላለው ጥሪ ፈጣን ምላሽ እንድትሰጡ ኦነግ በድጋሚ ጥሪውን ያስተላልፋል።

እራሴን እያደስኩ ኣገዛዜን መቀጠል ኣለብኝ በሚል የስርዓቱን ታማኞች እየሾመ ለውጥ ያደረገ ለማስመሰል ጥረት ላይ ያለው የወያኔ ፓርቲ በህዝቡ ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት ኣይኖረውም። ህዝቦች የይስሙላ ለውጥ ሳይሆን መሰረታዊ ለውጥ ይፈልጋሉ። በተለይ ደግሞ የኦሮሞ ህዝብ ሰውን በሰው መተካት ለውጥ እንደማያስገኝ ካሁን ቀደሞቹ ተመሳሳይ እርምጃዎች በቂ ትምህርትና ተሞክሮ ኣግኝቷል። ስለሆነም በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅ የሆኑ ቃላትን ተጠቅመን ህዝቡን ማታለል እንችላለን በሚል ኣፋቸውን ማር ቀብተው መርዝ በመርጨት ላይ የሚገኙትን በማስወገድ መብታችንን ከእጃችን ለማስገባት እንነሳ።

ኦነግ ለረጅም ዓመታት የጎረቤትና የውጪ መንግስታት በዲሞክራሲና በህዝቦች እኩልነት ሽፋን ወደ የለሽ ዝርፊያና ጭቆና እያካሄደ ያለውን የወያኔ መንግስት በኢኮኖሚ፣ በወታደራዊ ስልጠናና በዲፕሎማሲ እንዳይረዱ በተደጋጋሚ ጥሪውን ሲያስተላልፍ እንደነበር ይታወቃል። ይሁን እንጂ ይህንን የቀረበላቸውን ጥሪ በመተላለፍ እገዛቸውን መቀጠላቸው ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን ለማየት ተገደዋል። የወያኔ መንግስት ከጎረቤት ሃገራትና ከሌሎችም መንግስታት በሚያገኘው ድጋፍና እርዳታ የኦሮሞን ህዝብና የተቀሩትንም የኢምፓዬሪቷን ህዝቦች በሺዎች ከመሬታቸው ኣፈናቅሏል።
ይህ መንግስት በቢሾፍቱ የእሬቻ በዓል ላይ ያደረሰውን የጅምላ ፍጅትና በውጪ መንግስታት የሰለጠነውና የታጠቀው ጦር ሃይል በጨለንቆና በሌሎችም የኦሮሚያ ኣካባቢዎች በኦሮሞ ህዝብ ላይ የፈጸመው የጅምላ እልቂት በግልጽ ታይቷል። ይህንን ለመብቱ በሚፋለም ህዝብ ላይ የደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት እያዩና እየሰሙ ዝምታን መምረጥ የሚያስጠይቅ መሆኑን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ኣሁንም በድጋሚ ያሳስባል። ኦነግ እየተፋለመ ያለውን ጠላት መርዳታቸውን እንዲያቆሙ እንጂ ኣንዳችም እርዳታ ከነሱ እንደማይሻ ተረድተው ይህንን በህዝቡ ላይ ለሚደርሰው ፍጅትና ጉዳት ምክንያት እየሆነ ያለውን እገዛቸውን እንዲያቆሙ ይጠቃል። የኢትዮጵያ ኢምፓዬርን ኣንቆ የያዛት ችግር መፍትሄ ወያኔን በስልጣን ላይ በማሰንበትና በይስሙላ ለውጥ እንደማይገኝ እንዲያስተውሉ ኦነግ ኣበክሮ ያሳስባል።

የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ያለኣንዳች የውጪ እርዳታ በራስ ላይ በመመርኮዝ በሚካሄድ ትግልና በተከፈለው መስዋዕትነት ዛሬ የደረሰ ትግል ነው። ካሁን በኋላም ለነጻነትና ለሉዓላዊነት እያካሄድን ያለው ትግል ወደኋላ የማይመለስ መሆኑን እናረጋግጣለን። ይህንን ትግል ውጤታማ ለማድረግ ከኦሮሞ ህዝብ ውጪ ሌላ ኣንዳች የምንጠንቀው ኣጋር እንደሌለ በመገንዘብ በኣዲሱ ዓመት በጠላት ላይ ታላቅ ድል ለመጎናጸፍ እንድንንቀሳቀስ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የትግል ጥሪውን ያቀርባል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**

**ታህሳስ 31 ቀን 2017ዓም**